የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፱
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.89
ADDIS ABABA, 8st September, 2017

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፩/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለሻምቡ-አጋምሳ የመንገድ ስራ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……ገፅ ፱ሺ፱፻፮

CONTENT

Proclamation No.1041/2017

Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Shambu-Agamsa up grading Road Project Ratification Proclamation.................page 9906

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፩/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሻምቡ-አጋምሳ የመንገድ ስራ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፳ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ሀያ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአህመድሃባድ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## PROCLAMATION No.1041/ 2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMNT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

**WHERE AS,** a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa is stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 20,0000,0000 USD(twenty million United States Dollars) for Financing Shambu-Agamsa upgrading Road Project was signed in India (Ahmadadad) on the 24th day of May 2017;

**WHERE AS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 5th day of July 2017;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of the Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:



www.chilot.me

ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለሻምቡ-አጋምሳ የመንገድ ስራ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፩/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአህመድሃባድ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫.የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ሀያ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the " Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Shambu-Agamsa up grading Road Project Ratification Proclamation No.1041/2017"

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan agreement signed in India ( Ahmadabad) between the Federal Democratic Republic of Ethipopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 24th day of May 2017 is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 20,000,000 USD (Twenty Million US Dollars ) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of September, 2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

www.chilot.me